# ለአስተዳደር ሠራተኞች የድልድል ቅድመ ሁኔታዎች

- የትምህርት ዝግጅት ሆነ የስራ ልምድ ቀጥታና አግባብ ያለው/(100%) ብቻ ለድልድል ይያዝለታል፣
- አንድ ሠራተኛ በ2/ሁለት/ የስራ መደብ ላይ ብቻ መመዝገብና መወዳደር ይጠበቅበታል፣
- አንድ ተወዳዳሪ በሚያሟላበት የስራ መደብ ላይ ትክክለኛ የስራ ልምድ እና የትምህርት ዝግጅት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ መመዝገብ አለበት፤
- የጡረታ ጊዜያቸው የደረሰና ጡረታ ለመውጣት 3 ወርና ከዚያ በታች የቀረው መወዳደር የማይችል መሆኑን፤
- የሙከራ ቅጥር ጊዜውን ያላጠናቀቀ ሠራተኛ እንደሌሎች ቋሚ ሠራተኞች ለድልድል ውድድር በእጩነት ተመዝግቦ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር መወዳደር አይችልም፡፡ ነገር ግን በተቀጠረበት የሥራ መደብ ትይዩ ደረጃና ሲያሜ ላይ ይመደባል፣
- በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከደረጃ I እስከ ደረጃ V ሰልጥነው የምስክር ወረቀት ያቀረቡ ቋሚ ሠራተኞች ለዚህ ድልድል ለአንድ ጊዜ ብቻ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባይኖራቸውም ባላቸው የትምህርት ደረጃ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ሠራተኞቹ በመሥሪያ ቤታቸው ልዩ ድጋፍ ተደርጕላቸው የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃውን በቀጣይ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲያገኙ ክትትል ይደረጋል፡፡
- የመጀመሪያ ዲግሪ በሚጠይቁ የሥራ መደቦች ላይ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሠራተኞች እንዲወዳደሩ በሚፈቅዱ መመሪያዎች መሠረት ተመድበው በመሥራት ላይ ያሉ ሠራተኞች በዚህ ድልድል ወቅት በአንድ የሙያ የእድገት መሰላል ተዋረድ I እና ተዋረድ II የሥራ መደቦች ላይ ተወዳድረው መመደብ ይችላሉ፡፡
- እስከ 2ኛ ዓመት ኮሌጅ ድረስ ያሉት የትምህርት ደረጃዎች ከመፈጸማቸው በፊትም ሆነ በኂላ፣ የተገኘው የሥራ ልምድ ከሥራው ጋር አግባብ ያለው ከሆነ በግማሽ ይታሰባል፡፡
- በድልድል ወቅት የመጀመሪያ ዲግሪ በሚጠይቅ የሥራ መደብ ላይ ዲፕሎማ ያለው ሠራተኛ ሊደለደል የሚችለው ዲፕሎማ ካገኘ ወይም የ3ኛ ዓመት ትምህርት ካጠናቀቀ በኂላ የተገኘ አግባብ ያለው የአንድ ዓመት የሥራ ልምዱን እንደ አንድ ዓመት በመያዝ ነው፡፡
- በአካዳሚክ ቅጥር የተቀጠራችሁ ሠራተኞች በአስተዳደር መደቦች ላይ መወዳደር የማትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
- ከዘጠኝ ወር ወዲህ የደረጃ እድገት አግኝተው የመቆያ ጊዜያቸውን ያልጨረሱ ሰራተኞች በሚያሟሉበት የስራ መደብ ላይ ተመዝግበው መወዳደር ይችላሉ፡፡
- ከነባር የሥራ መደቦች ደረጃ አንጻር ዝቅ ካለ የሥራ መደብ ከፍ ወዳለ የሥራ መደብ በሙከራ ትግበራ ለተደለደለ ሠራተኛ የነበር ሥራ መደቡን ደረጃ ደመወዝ መክፈል አይፈቀድም፡፡
- የኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት የሰጠውን ሥልጠና የወሰዱና ብቃታቸው ግምገሞ የሚመደቡበትን ደረጃ ወስኖ ሲልክ የሚደለደሉ ይሆናል፣
- በኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ሥልጠና ሳይወስዱ በተለያዩ በጽ/ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች እንደማንኛውም ሠራተኛ በሚያሟሉበት ሥራ መደብ እየተወዳደሩ ሊመደቡ ይችላሉ

## የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት